# ሀቅን ፍፁም ለመሸምጠጥ ቢያንስ በጊዜው የነበሩት እማኞች በሙሉ እስኪሞቱ መጠበቅ፡ የቅንጅት አመራር ከእስር የተፈቱበትን አካሄድ በተመለከተ የነበረውን እውነት ለኢትዮጵያውያን ለማሳየት የቀረበ አጭር ሪፖርት፡፡

ብርሃኑ ነጋ
ሙሉነህ እዩኤል
አንተነህ ሙሉጌታ

ውሸታም ሰው ከተራ ውሸታምነት ወደ ተመሰከረለት የአእምሮ በሽተኛነት (pathological liar) የሚቀየርበት ጊዜ መቼ እንደሆነ ትክክለኛውን ጊዜ በእርግጥ ባናውቀውም፡ እራሱ የፈጠረውን ውሸት ከልቡ ማመን ሲጀምርና ሌላው ሁሉ እንደሱ እንዲያምነው ሲጥር አልፎም በጊዜው የነበሩ፣ የሱን ውሸት ተራ ፈጠራ መሆኑን የሚያውቁ ጤነኛ ሰዎችን ‹ውሸቴን ካልተቀበላችሁ› ብሎ ችክ ማለት ወይም መጣላት ሲጀምር ይመስለናል፡፡ መለስና በረከት እንዲሁም በአካባቢያቸው የተሰበሰቡ ጥቂት ‹እነሱ ያሉትን አዎንና እሽ› ማለትን ኑሮ አድርገው የያዙ ደካሞች እዚያ የህመም ደረጃ ከደረሱ ትንሽ የሰነባበቱ ቢሆንም ከሰሞኑ የቅንጅት መሪዎችን አፈታት በተመለከተ ወይዘሪት ብርቱካንን ‹የጎነጎንነውን ውሸት እውነት ነው ብለሽ ካልተቀበልሽ› ብለው ዘብጥያ የማውረዳቸውን ተአምር ለተከታተለ፡ ሰዎቹ በእርግጥም እውነትና ውሸት፣ ክፉና በጎ፣ ቀኝና ግራ፣ የተምታታበት ድቅድቅ የአእምሮ መቀመቅ ውስጥ መግባታቸውን ሊስተው አይችልም፡፡[i]

እንዲህ አይነት የአእምሮ በሽታ የተጠናወታቸው ሰዎች ዝም ብለው በራሳቸው የውሸት አለም ውስጥ ቢኖሩና ሌላውን ባይነኩ እንደማንኛውም የአእምሮ በሽተኛ አዝነንላቸው፣ ከንፈራችንን መጠን እንተዋቸው ነበር፡፡ ይህ በሽታ የተጠናወታቸው ሰዎች ከራሳቸው አልፈው ሌሎችን ጤነኛ ሰዎች መጉዳት ሲጀምሩ፣ ወይም ደግሞ እንደኛዋ ባልታደለች አገር በአጋጣሚ እነኝህ ሰዎች ምንም ያልተገደበ የመንግስት ስልጣን ላይ ተቀምጠው ማህበረሰቡን በሙሉ እነሱ በፈጠሩት የውሸት አለም ውስጥ እንዲኖር ማስገደድ ሲጀምሩ፣ በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ የሚፈጥሩት አደጋ በጣም ዘላቂና ብዙ መዘዝ ያለው ስለሚሆን ይህን እያዩ ዝም ብሎ መቀመጥ የነሱ የጥፋት ተግባር አካል መሆን ነው የሚሆነው፡፡ በአደጋ ላይ ያለው የአንድ ጊዜ ‹ወዲያ ተወው› ተብሎ በንዝህላልነት የሚተው ውሸት ሳይሆን የዚያን ማህበረሰብ ምንነት፡ ማህበረሰቡን የሚያስተሳስረውን የሞራል ሰንሰለት የሚበጥስ በጣም አደገኛ ሁኔታ ነው የሚፈጥረው፡፡ ለዚህ ነው በዚህ ጉዳይ ላይ በተለይ የጉዳዩ ባለቤቶች ነን ብለው ሲሸለሙ የነበሩ፣ የነበረውን ሁኔታ ለህዝቡ የምንናገረው እኛና እኛ ብቻ ነን፣ በጉዳዩ ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊዎች የነበራችሁት (የቅንጅት መሪዎችና የመንግስት አካላት) በጉዳዩ ላይ ምንም መግለጫ አትሰጡም ብለው የድርድሩ አካል ያደረጉት ‹ሽማግሌዎች› አንዲት ቃል ለመተንፈስ መፍራታቸው በጣም የሚያስገርመውና የሚያሳፍረው፡፡ እነመለስ ፊርማው ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የውሸት ፕሮፓጋንዳቸውን ሲደረድሩ ተዉ ማለት አቅቶአቸው ነገሩን ይኸው የመጀመሪያውን ንፁህ ሰው እንዲበላ ፈቀዱለት፡፡ የዚህ የውሸት ድሪቶ እዳ ግን ገና የሚለቀን አይደለም፡፡ ስለዚህ እነሱ ይህን ሀላፊነታቸውን ለመወጣት ምንም የቀረ ለእውነት ለመቆም የሚያስችል እንጥፍጣፊ ወኔ ከሌላቸው፣ ሀላፊነቱ በጊዜው የነበረውን የሚያውቅ ማንኛውም የእውነት ወገንተኛ ነው የሚሆነው፡፡

ይህን ለእውነት ያለንን ሀላፊነት ለመወጣትም ነው በጊዜው የነበረውን ሁኔታ፣ ቢያንስ እኛ የድርድሩ አካል ሆነን የምናውቀውን፣ ሽማግሌ ተብየዎቹ ‹ከጠቅላይ ሚኒስቴሩ ጋር ተገናኝተን ያገኘነው መልስ› እያሉ በየጊዜው ለሚነሱ ጥያቄዎች ይሰጡን የነበረውን መልስ በመንተራስ፣

በጊዜው የሆነውን እንዳለና እንደወረደ ለማህበረሰቡ ማሳወቅ ተገቢ ነው ብለን ይህን አጭር ፅሁፍ በኦፌሴል ለማህበረሰቡ ለማቅረብ የወሰንነው፡፡ ይህን ስናደርግ አንድ መሰረታዊ የሆነ ታሳቢ ያደረግነው ነገር አለ፡፡ ይኸውም ሌላ ቢቀር ሽማግሌዎቹ የነመለስ የውሸት አካል ሆነው ከመጀመሪያ ጀምሮ ሆን ብለው ሲዋሹ አልነበሩም ብለን አምነናል፡፡ ይህም ማለት መጥተው ለኛ የሚነግሩን ቢያንስ እነመለስ ንገሩ የሚሉዋቸውን እንጂ (ቢያንስ የተወሰኑቱ) ዝም ብለው ያልተባሉትን በራሳቸው ፈጥረው ይዋሻሉ ብለን እስከአሁን አናምንም፡፡ እንደዚያም አድርገው ከሆነ፣ ማለትም ሽማግሌዎቹ የነመለስ የውሸት ተባባሪ ብቻ ሳይሆን እራሳቸውም ውሸት ፈጣሪ (እኛን ብቻ ሳይሆን እነመለስንም ዋሽተው ማለት ነው) ቢሆኑ እንኳዋን፣ እኛ በምንፈታበት ሁኔታ ላይ አውቀን ከወሰንነው ውጪ ላለው ተጠያቂ አይደለንም፡፡ ምክንያቱም ለውሳኔያችን መሰረት የሆነው የተነገረን መረጃ ስለሆነ፡፡ ብርቱካን ለመፈታታችን ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ስታቀርብ እሱዋ በሽማግሌዎች የተነገሩንን ነገሮች መነሻ አድርጋ ነው፡፡ ይህ እሱዋ ያለችውና እኛም የምናቀርበው መረጃ በነመለስ አይን ውሸት ሊሆን የሚችለው፣ ሽማግሌዎቹ እኛንም እነመለስንም የዋሹ እንደሆን ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሊሆን እንደማይችል አንባቢው ለመገመት ይቸግረዋል ብለን አናምንም፡፡ ከምናቀርበው እንደምናሳየው፣ የሆነውን ሁሉ እነመለስ ያቀነባበሩት መሆኑን ለማሳየት ከባድ አይደለም፡ ጤነኛ አእምሮ ላለው ሰው፡፡

1. *መነሻ መረጃዎች፡*

- *ሽማግሌዎቹ ከቅንጅት መሪዎች ጋር በኦፌሴል ውይይት የጀመሩት የቅንጅት እስረኞች ገና ከማእከላዊ ወጥተን ቃሊቲ ከደረስንበት ወቅት ጀምሮ ነው፡፡ ይህም ማለት ታህሳስና ጥር* 1998 *አ.ም. አካባቢ ማለት ነው፡፡ ይህ እንግዲህ ገና ማእከላዊ እያለን ‹እስረኞቹን ለመጠየቅ› ብለውና በየክፍላችን መጥተው ለመጠየቅ የቻሉበትን ጊዜ ሳንቆጥር ነው፡፡ በጥቅሉ ወደ* 18 *ወራት የፈጀ ድርድር ነበር ማለት ነው፡፡*
- *ምንም እንኳዋን በተለያየ ጊዜ የተቀያየሩ ሰዎች ቢኖሩም ከሞላ ጎደል በቋሚነት ጉዳዩን ሲከታተሉ የነበሩትና በአብዛኛው ውይይት ላይ የተሳተፉት* 1) *ፕ/ር ኤፍሬም ይስሀቅ (የቡድኑ መሪ)* 2) *ፓስተር ዳንኤል ገ/ስላሴ (ከቡድን መሪው ቀጥሎ ዋናው ተዋናይ)* 3) *አትሌት ሀይሌ ገ/ስላሴ* 4) *አምባሳደር በቀለ እንደሻው ናቸው፡፡ በስተመጨረሻው ላይ ነገሩ የሕግ ትርጉዋሜ ያስፈልገው እንደሆን በሚል* 5) *ጠበቃ ታምሩ ወንድማገኝሁ የሽማግሌ ቡድኑን ተቀላቅሎአል፡፡*
- *ምንም እንኳዋን በመጀመሪያው ላይ ከመንግስት ጋር የሚደረገውን ግንኙነት የቡድኑ መሪው ብቻውን ከመለስ ጋር በመገናኘት እንደሚያደርገው ሲገልፅ ቢቆይም በተለይ በአንዳንድ የቅንጅት ተደራዳሪዎች በኩል የነበረውን ያለማመን ስሜት ለማርገብ በሚመስል (ከአንዳንድ የሽማግሌ ቡድኑ አባላት በቀረበ የቅሬታ አስተያየት መሰረትም) ሌሎቹ የሽማግሌ ቡድኑ አባሎች በተለያየ ጊዜ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር መገናኘታቸውን አረጋግጠዋል፡፡ ለማንኛውም በመንግስት በኩል ‹ስምምነት ተደርሶባቸዋል› የተባሉት ጉዳዮች በሙሉ በቡድኑ መሪው በኩል በቀጥታ ከመለስ የመጡ መሆናቸው ለቅንጅት ተደራዳሪ ቡድን እየተነገረው ነው ድርድሩ የቀጠለው፡፡ (መለስና በረከት ይህንን ሽማግሌዎቹን እራሳቸውን ቢክዱዋቸው ግን ምንም አይገርመንም)*

2. **መሰረታዊ ጭብጦች**

- ሽማግሌዎቹ ‹ድርድሩን› የጀመሩት ባጠቃላይ አገሪቱ ወደ አደገኛ ሁኔታ እያመራች ነውና የተፈጠረውን ችግር ‹በይቅር መባባል መንፈስ› ፈትቶና የቅንጅት መሪዎችን ከእስር አስወጥቶ በቶሎ በቀጥታ ከመንግስት ጋር የአገሪቱን የወደፊት የፖለቲካ አካሄድ በተመለከተ ቀጥተኛ ውይይት እንዲደረግ ከሚል ነበር፡፡ በሌላ አነጋገር የእስረኞቹ መፈታት ለሚደረገው ዋና የፖለቲካ ድርድር እንቅፋት ስለሆነ እሱን ለመጥረግና አገሪቱን ወደ ዴሞክራሲ የሚያሸጋግረው ውይይት በአስቸኳዋይ እንዲጀመር ከሚል የተጀመረ እንጂ፣ የእስረኞቹ መፈታት በራሱ ግብ ነው ተብሎ የተጀመረ አልነበረም፡፡
- ሽማግሌዎቹ ለድርድር ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ በቅንጅት ተደራዳሪዎች በኩል ሽማግሌዎቹ የነመለስ መጠቀሚያ ሊሆኑ ይችላሉ የሚለው ሀሳብ በሰፊው ነበር፡፡ እነመለስ የሚታመኑ እንዳልሆኑ፣ ተራ የማጭበርበር ስራ ለመስራት የማይመለሱ ምንም የሞራል ለከት የሌላቸው እንደሆኑ፣ አሁንም ይህንን ውይይት በቀናነት ያደርጉታል ለማለት እንደማይቻል፣ ሁሉን ነገር ከአጭር ጊዜ የፖለቲካ ትርፍ አንፃር እንጂ የዘለቄታ የአገር ጥቅም የሚል ነገር ከስሌታቸው እንደማይገባ፣ ከዚህ በፊት ከነሱ ጋር ያደረጉዋቸውን ድርድሮች ዋቢ በማድረግ ገልፀውላቸዋል፡፡ በተለይ የሽማግሌዎቹ ቡድን መሪ እነመለስ የተቀየሩ እንደሆኑ፣ አሁን ያሉበት ችግር ግዝፈት በደንብ የታያቸው እንደሆነ፣ ከልባቸው ይህንን ችግር ለዘለቄታው መፍታት እንደሚፈልጉ እየተማለ እየተነገራቸው፣ ግን ጥርጣሬአቸውን እንደያዙ ነበር ድርድሩን የቀጠሉት፡፡
- በዚህም መሰረት ‹ድርድሩ› ያተኮረው ይህንን የሽግግር ሁኔታ በምን መልክ እናመቻቸው የሚል ሆኖ ከብዙ ውይይትና ክርክር፣ በቡድኑ መሪ ከአራት ኪሎና ቃሊቲ መመላለስ፣ (እንዲሁም በፓስተር ዳንኤል የሚመራ ፀሎት) በሁዋላ 8 ነጥቦችን የያዘ ‹ስምምነት› ላይ ተደረሰ፡፡ ምንም እንኩዋን ስምንቱን ነጥቦች እንዳሉ ማስታወስ ባንችልም የሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች ይገኙባቸዋል፡

ሀ) የቅንጅት መሪዎች እንደተፈቱ ባስቸኩዋይ፣ በሶስተኛ ወገን አደራዳሪነት በአገሪቱ የፖለቲካ ሂደት ላይ ሁሉንም የፖለቲካ ቡድኖች ያሳተፈ ድርድር እንዲጀመር

ለ) መንግስት በሰኔና በጥቅምት ለሞቱት ወገኖች ይቅርታ እንዲጠይቅና ለቤተሰቦቻቸውም ተገቢውን ካሳ እንዲከፍል

ሐ) የቅንጅት መሪዎች የምርጫውን መጭበርበር ተከትሎ ለተፈጠረው ሁከትና በንብረትና በሰው ሕይወት ላይ ለደረሰው አደጋ ሀዘናቸውን እንዲገልፁ፣ ችግሩ እንዳይከሰት ለማድረግ ባለመቻላቸውም የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንዲጠይቁ

መ) የፖለቲካ ድርድሩ እየተካሄደ እያለ ቅንጅት እንደ ፖለቲካ ድርጅት ከፈለገ "አገኛቸው የተባለውን" የፓርላማ መቀመጫዎች ይዞ ፓርላማውን እንዲቀላቀል፣ የአዲስ አበባ ከተማን ተረክቦ እንዲያስተዳድር፡

ሠ) በፖለቲካ ምክንያት የታሰሩት በሙሉ እንዲፈቱና የተጀመረ ማንኛውም የፍርድ ሂደት እንዲቋዋረጥ

ረ) ሁሉም የፖለቲካ ሀይል፣ መንግስትን ጨምሮ፣ ለሕገመንግስቱ ተገዢ እንዲሆኑ፣ የፖለቲካ ልዩነቶች በሕገ መንግስቱ ጥላ ስር እንዲፈቱ፣ የሕግ የበላይነትን የማክበርና የማስከበር የሁሉም ሀላፊነት እንደሆነ...ወዘተ የሚሉና የመሳሰሉ ነበሩ፡፡

- ይህ ባለ 8 ነጥብ የስምምነት ሀሳብ (በመጀመሪያ ሽማግሌዎቹ ይዘውት ከመጡት ሀሳብ ላይ በመንደርደር) ተረቆና በቅንጅት መሪዎችና በሽማግሌዎች ከታመነበት በሁዋላ፣ የቡድን መሪው የስምምነት ሀሳቡን ይዘው አራት ኪሎ ሄደው ከሁለት ቀናት ያክል ቆይታ በሁዋላ

በመመለስ ጠ/ሚሩ በሁሉም ነጥቦች ላይ መስማማታቸውን፤ የአንዳንዱን ሀሳብ እንዲያውም የበለጠ አሻሽለው እንዳስቀመጡትና ይህ ስምምነት ሊፈረም እንደሚችል፤ ሆኖም ግን በቅንጅት መሪዎች በኩል የሚቀርበውን ይቅርታ በተመለከተ ለመንግስትም ትንሽ የመውጪያ በር (አንዳንዶች የወንድ በር ነበር የሚሉት) ስለሚያስፈልግ ትንሽ ተስፋፍቶ መቀመጥ አለበት በሎአል፤ ስለዚህ ስምንቱ ነጥቦች እንዳለቀላቸው ተቆጥሮ ይቅርታውን በሚመለከት ግን ትንሽ የተፍታታ ነገር ይቀረፅ የሚል ሀሳብ ያቀርባሉ፡፡

- ያ የሚቀረፀው ነገር ምን እንዲያካትት እንደሚፈለግ የቀረበ ሀሳብ እንዳለ ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ፤ አንድ ፓራግራፍ የሚሆን ፅሁፍ የቡድን መሪው ‹ከዚያው ያገኙት› በሚል ያቀርባሉ፡፡
- የቅንጅት ተደራዳሪዎች ያንን አንቀበልም ብለው በምትኩ ሌላ የራሳቸውን ፓራግራፍ ያዘጋጃሉ፡፡ ከብዙ ውጣ ውረድና የቃላት ጨዋታ በሁዋላ በቀረበው የመጨረሻ ድራፍት ሽማግሌዎቹም ተስማምተው፤ ከቅንጅት ተደራዳሪዎቹም ሁለት አባላት ፊርማቸውን አኑረውበት ይሄዳል፤ ይህ ፅኁፍ እንግዲህ ባለ 8 ነጥብ ስምምነቱ እንዳለ ሆኖ ማለት ነው፡፡
- በነጋታው ወይንም በሁለተኛው ቀን የሽማግሌዎቹ ቡድን መሪ ‹ስምምነት ተደረሰ› ብለው የእስረኞቹን በሙሉ ሊስት የያዘ የመፈረሚያ ሰነድ ተዘጋጅቶ፤ በሙሉ በተራ እየወጡ ይህንን ፓራግራፍ እንዲፈርሙበት ይጠይቁና ከተለያዩ ዞኖች እስረኞች ወደ ቢሮ በተራ ተጠርተው ይሄዳሉ፡፡
- በመጀመሪያ ከዞን አንድ የሄዱት እስረኞች ሰነዱን ሲያዩት ያ ስምምነት ተደረሰበት የተባለው ፓራግራፍ ሳይሆን ከዚያ በፍፁም የተለየ፤ የረብሻውን ችግር በእስረኞቹ ላይ የሚደፈድፍ ሆኖ ይገኛል፡፡ ሁሉም እስረኞች ይህንን ሲያዩ አንፈርምም ብለው ወደእስር ቤት ይመለሳሉ፡፡ **ሁላችንንም ያስገረመን ግን መንግስት ስልጣን ላይ የተቀመጡት ሰዎች ምን አይነት ተራ አጭበርባሪዎች እንደሆኑ ነው፡፡ ይህንን ተራ የቅጥፈት ስራ ያውቁ እንደሆን የሽማግሌዎቹ ቡድን መሪ ቢጠየቁ፤ እሳቸው ልብ ብለው እንዳላዩትና አጣርተው እንደሚመለሱ ተናግረው ይሄዳሉ፡፡ ከዚያ በሁዋላ ምን እንደሆነ ሳይናገሩ ወደመጡበት አገር ይመለሳሉ፡፡ ለብዙ ወራት ተመልሰው አልመጡም፡፡ አሁን ወደሁዋላ ተመልሰን ስናየው የሽማግሌ ቡድኑን የመሩት ሰውዬ አላወቁትም ለማለት ይከብዳል፡፡**
- ከብዙ ወራት በሁዋላ ተመልሰው ሲመጡ የፍርድ ቤት የጨዋታ ሂደቱ አንድ ደረጃ ላይ ደርሶ፤ ተከሳሾቹ ‹ተከላከሉ› ተብለው እንከላከል አንከላከል የሚለው ውሳኔ ላይ ከመድረሳቸው በፊት ከፍርድ ቤቱ ለመከላከል የሚያስፈልጉዋቸውን ዶኩመንቶች (የፍርድ ቤት ትራንስክሪፕት፤ የምስክሮች ቃል…ወዘተ) እንዲሰጣቸው ፍርድ ቤቱን ሲጠይቁ፤ በጉዳዩ ላይ (ማለትም ዶኩመንቶች ይሰጡ አይሰጡ በሚለው ላይ) ብይን ለመስጠት ዳኞቹ (አዲል አህመድ፤ ልኡል ገ/ማሪያምና መሀመድ አሚን ሳኒ) ለ10 ደቂቃ ጊዜ ስጡን ብለው ሄደው ለሁለት ሰአት ቆይተውና ከበላይ መመሪያ ተቀብለው ከመጡ በሁዋላ ብይን መስጠቱን ትተው ‹በተከሰሳችሁበት ክስ ጥፋተኛ ሆናችሁ ተገኝታችሁዋል› የሚል፤ አስገራሚ ፍርድ ከሰጡ በሁዋላ፤ ቅጣት ለመወሰን ቀጠሮ ይዘው ነበር፡፡
- በዚህን ጊዜ ነበር የሽማግሌዎቹ ቡድን አቶ ታምሩን ጨምሮ መምጣት የጀመረው፡፡
- ያኔ በሽማግሌዎች የሚቀርበው ነጥብ ‹እንደምታዩት ከፍ/ቤቱ ምንም ፍትህ ልታገኙ አትጠብቁም› በመንግስት በኩል አሁንም በዚያ ‹ቀደም ሲል አንፈርምም ባላችሁት የይቅርታ ሰነድ ላይ ከፈረማችሁ› አሁንም ክሱን አቋሞና ዘግቶ፤ ቀድሞ በተስማማችሁበት ባለ ስምንት ነጥብ (በሁዋላ ተሸጋሽጎ አምስት ነጥብ ሆኖ ነበር) ድርድር ውስጥ በቀጥታ መግባት ይፈልጋል፡፡ ምናለ ለመንግስት ‹የወንድ በር› የማትሰጡትና ይህ ነገር የማያልቀው

በሚል ፅኑ ልመና የተደረገበት ጊዜ ነበር፡፡ (የሽማግሌ ቡድኑ መሪ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ላይ እግር ላይ ወድቆ መለመን፣ እንባ ማፍሰስ…ወዘተ ምንም አይቸግራቸውም ነበር)

- ከዚህ በተጨማሪም ሽማግሌዎቹ እናንተ ይቅርታ የምትጠይቁት በሽማግሌዎቹ በኩል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡፡ ይህንን ደብዳቤ ከኛ በቀር ማንም አያየውም፡፡ ጠ/ሚሩ እራሳቸው ‹ይህንን ፈርመው ለናንተ ከሰጡ እኔም ሳላየው በምትኩ ክሱን የማሰረዝ.ያውንና ከእስር የመፈቻውን ደብዳቤ ያንኑ እለት እሰጣችሁዋለሁ› ብለውናል፡፡ ይህንንም እናምናቸዋለን፡፡ በሕግ በኩልም ይህ ነገር አሁን ካለቀ የይቅርታ ፍቺ ሳይሆን ክሱ ተሰርዞ የሚደረግ ፍቺ ነው ብለው፣ ይህንኑ ይዘዋቸው የመጡት የሕግ ባለሙያ አረጋግጠው፣ ይህ የነሱ ስሜት ሳይሆን ከመለስ ከራሱ የተነገራቸው መሆኑን ደጋግመው ተናግረዋል፡፡ ተደራዳሪዎቹም ይህንን ጉዳይ እኛ የምንወስነው ሳይሆን ሁሉም እስረኞች (ቢያንስ አመራሩ በሙሉ) ተገኝቶ የሚወስነው ስለሆነ ስብሰባ እንድናደርግ አስፈቅዱልን ብለው ጠይቀው፣ በዚያ መሰረት አስፈቅደው ከሁለት ቀናት በሁዋላ ለውሳኔው ይመጣሉ፡፡

3. **የመጨረሻዎቹ ሁለት ሳምንታት፡**

- የቅንጅት አመራር አካል በዚህ ጉዳይ ላይ ለሁለት ቀናት ከተከራከረና ከወሰነ በሁዋላ ከሽማግሌዎቹ ጋር እንደገና ተገናኝቶ ስለውሳኔው አፈፃፀም ውይይት ያደርጋል፡
- በዚህ ውይይት ላይ ስለውሳኔውና ስለአፈፃፀሙ የሚከተሉት ግልፅ ስምምነቶች ከሽማግሌዎቹ (እንዲሁም በሽማግሌዎቹ በኩል ከመንግስት) ጋር ይደረሳል፡፡ እነኝህም፡

ሀ) የይቅርታ ደብዳቤው የአጠቃላይ ስምምነቱ አካል ነው፡፡ የይቅርታ ደብዳቤውም የሚቀርበው ለአገር ሽማግሌዎች በሚል ነው፡፡ የአገር ሽማግሌዎች ይህን ይዘው የራሳቸውን ደብዳቤ ለመንግስት ይፅፋሉ እንጂ ይህ የተፈረመ ደብዳቤ ለመንግስት አይሰጥም
ለ) ይህ ወረቀት በተፈረመ በሁለት ቀናት ውስጥ ክሱ ተሰርዞ እስረኞቹ ይፈታሉ
ሐ) እስረኞቹም ሆነ መንግስት ፍቺውን በተመለከተ ለሕዝብ ምንም መግለጫ አይሰጡም፡ ሽማግሌዎቹ የእለቱ ለት በይቅርታ መባባል መንፈስ ጉዳዩ እንደተፈፀመና ቀጣይ ድርድር እንደሚካሄድ ለሚዲያና ለሕዝብ ጋዜጣዊ መግለጫ ይሰጣሉ
መ) መንግስትም ሆነ የቅንጅት መሪዎች ይህን ጉዳይ ለሉታዊ ለሆነ ፕሮፓጋንዳ አይጠቀሙበትም
ሰ) በዚህ ስምምነት በቀጥታ ከሚፈቱት ውጪ በሌሎች እስር ቤቶች የሚገኙ ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ የታሰሩ እስረኞች በሙሉ በዚህ ስምምነት መሰረት ይፈታሉ፡፣

- በነኝህ ጉዳዮች ላይ ግልፅ ስምምነት ከተደረሰ በሁዋላ የቅንጅት አመራር በመጀመሪያ ይህንንው ‹ለአገር ሽማግሌዎች› በሚል የተፃፈ ደብዳቤ ይፈርማሉ፡፡
- አመራሩ ፈርሞ እንደጨረሰ ጊዜው ስለመሸ ሌሎቹ ታሳሪዎች በነጋታው እንደሚፈርሙ ስምምነት ተደርሶ፣ የቡድን መሪው እራሳቸው መጥተው ሁሉንም እንደሚያስፈርሙ ቃል ገብተው ይሄዳሉ፡፡

**ከዚህ ቀን ጀምሮ አዲሱ የነመለስ ተራ የአጭበርባሪነት ስራ ይጀመራል፡፡ ይህንን ወህኒ ቤት ቁጭ ብለን በቴሌቪዥን ስንከታተል ይገርመን የነበረው የምናየው ግልፅ የማጭበርበር ሂደት**

*የሚፈፀመው ከአንድ የሰፈር ዱርዬ እንጂ በመንግስት መሪዎች ነው የሚደረገው ብሎ ለማመን በጣም የሚቸግር ነበር፡፡ ሁኔታው እንዲህ ቀጠለ፡*

- *በነጋታው ተመልሰው መጥተው ቀሪዎቹን ታሳሪዎች መሪዎቹ ከፈረሙት በተለየ ‹ለጠ/ሚሩ› በሚል የተፃፈ ግን ይዘቱ አንድ የሆነ ደብዳቤ ያስፈርሙዋቸዋል (ይህንን የሽማግሌው ቡድን መሪ ሳያውቁት ነው ለማለት ይከብዳል፤ እነመለስ ሽማግሌዎቹን አጭበርብረዋቸው ሊሆን ግን ይችላል)፡፡ የፊርማው ጉዳይ በዚሁ ያልቃል፡፡*
- *ከሁለት ቀናት በሁዋላ ክሱ ይሰረዛል የተባለው ቀርቶ መለስ ለፓርላማ ‹በከተማው ስለሚወራው ወሬ ቁምነገር አትስጡ› የይቅርታ ጉዳይም ቢሆን የሚታየው ‹የፍርድ ሂደቱ ካለቀ በሁዋላ› መሆኑን ‹በኩራት› ይገልፃል፡፡*
- *የዚያኑ እለት የሽማግሌዎቹ ቡድን መሪ ብቻውን ቃሊቲ መጥቶ የድርድር ቡድኑን ሁለት አባላት ቢሮ አስጠርቶ ‹ጠ/ሚሩ ሄደህ እንኩዋን ደስ አላችሁ በላቸው ስላለኝ ነው› የመጣሁት፡፡ ጉዳዩ አልቁአል፡፡ አንዳንድ ማለቅ ያለባቸው ነገሮች ስላሉ ነው ዛሬ ያልተፈታችሁት…ወዘተ ይላል፡፡ ከተጠሩት ሁለት ሰዎች አንዱ ‹አሁንም አታፍርም? የነኝህ ሰዎች መሳሪያ ሆነህ ስታገለግል ቆየህ፡ ለራስህ ትንሽ ክብር ካለህ እንደዚህ የተራ ዱርዬ ስራ ሲሰሩ፤ የዚህ አካል አልሆንም ብለህ ጥለህ ትሄድ ነበር› ብሎት 5 ደቂቃም ሳይቆዩ ጥለውት ወደ እስር ቤታቸው ተመለሱ፡፡ ከዚህ ቀን በሁዋላ እስከ ፍቺው ቀን ማታ ድረስ እኝህን የሽማግሌ ቡድን መሪ ማንም እስረኛ አላያቸውም፡፡*
- *ከዚህ በሁዋላ የመጨረሻው የቅጣት ቀን እስከሚደርስ ዝም ይባልና ፍርድ ቤቱ በቀጠሮው ቀን የታዘዘውን በመሪዎቹ ላይ የእድሜ ልክ እስራቱን፤ በሌሎቹም ላይ እንዲሁ ከጥቂት አመታት እስከ እድሜ ልክ እስራት ይወሰናል፡፡*
- *ከዚህ ቀን ማግስት ጀምሮ የመንግስት መገናኛ ብዙሀን የቅንጅት አመራሮች ስለጠየቁት ‹የይቅርታ ደብዳቤ› ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ይጀምራል፡፡*
- *ፍርዱ ከተፈረደ ከጥቂት ቀናት በሁዋላና ፕሮፓጋንዳው ለሁለት ቀናት አየሩን ከሞላው በሁዋላ፤ ሶስት ሰዎች ያሉት ቡድን ቃሊቲ መጥቶ ከመሪዎቹ ውስጥ ግለሰቦችን ለብቻቸው ጠርተው ለማናገር ይሞክራሉ፡፡ ከነኝህ ውስጥ አንዱ የዚህ ፅሑፍ አዘጋጅ ስለሆነ ከሱ ጋር የተደረገውን ንትርክ በዝርዝር እናቀርባለን፡፡ በሌላ በኩል ለብቻ የተጠራው ሰውም በተመሳሳይ አታካሮ መለያየቱን ከወጣን በሁዋላ አረጋግጠናል፡፡*
- *ከወንድ እስረኞች ውስጥ በመጀመሪያ የተጠራው ዶ/ር ብርሃኑ ነበር፡፡ እዚያ ካገኛቸው ሶስት ሰዎች መሀከል ከአንዱ በቀር ሁለቱን አያውቃቸውም፡፡ አንደኛው ግን ሌላ ኮፍያውን አድርጎ የመጣው የሽማግሌው ቡድን ዋና አባል ፓስተር ዳንኤል ነበር፡፡ ‹እንዴ አሁንም አታፍርም? አንተ አሁን የሀይማኖት አባት ነኝ ብለህ ነው ፓስተር የምትባለው…ወዘተ የሚል ሀይለኛ ቁጣ የተሞላው ነገር ይናገረዋል፡፡ እሱም ‹ዶ/ር ብርሃኑ፡ ምንም ብትለኝ አልፈርድብህም፤ በውነትም የሚያሳፍር ነገር ነው፡ እኔም አልመጣም ብዬ በግድ ነው የመጣሁት፤ የይቅርታ ቦርድ አባል ስለሆንክ መሄድ አለብህ ብለው በግድ ነው ያመጡኝ፤ እኔ ራሴ አገሩን ትቼ ለመሄድ ተዘጋጅቻለሁ፤ ይህ በጣም አሳፋሪ ነው…ወዘተ› አለ፡፡ ያን ጊዜ ነው ዶ/ር ብርሃኑም ይህ የ ሶስት ሰዎች ቡድን የይቅርታ ቦርድ የሚባለው አካል መሆኑን ያወቀው፡፡ አንደኛው አሰፋ ካሲቶ (የፍትህ ሚኒስቴር) ሁለተኛው ደግሞ ፕሮፌሰር መስፍን የሚባል ሰው ነበር፡፡ ከእኔ ምን ጉዳይ አላችሁ ብሎ ዶ/ር ብርሀኑ ሲጠይቃቸው፤ አይ ይቅርታ ጠይቃችሁዋል የሚባለውን ሰምተን ለማረጋገጥ ነው የመጣነው አሉ፡፡ እንዴ፤ እኛ ለይቅርታ ቦርድ ያስገባነው ጥያቄ*

አለ እንዴ? ወይንስ ይህ ውሸታም መንግስት እንደለመደው አዲስ ቅጥፈት እያመጣ ነው? ለመሆኑ ፓስተር ዳንኤል አንተ እዚህ ነገር ውስጥ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ነበርክ አይደል እንዴ? ለምን ለአንዴ እንኳዋን እውነቱን አትነግራቸውም? ብሎ ሲጠይቅ ፓስተር ዳንኤል አቀርቅሮ አንገቱን ከመነቅነቅ በቀር የሚለው አልነበረም፡፡ በመጨረሻም አሰፋ ካሲቶ ‹ይቅርታ አልጠየቅክም ማለት ነው›? ብሎ ሲጠይቀው፡፡ እኔ ለይቅርታ ቦርድ ይቅርታ አልጠየቅኩም፤ ለይቅርታ ቦርድማ ይቅርታ ብጠይቅ ኖሮ ፎርሙን ሞልቼ የምልከው ላንተ አልነበረም እንዴ? መቼም ፎርሙን ታውቀዋለህ: ከማናችንም እንዲህ አይነት ፎርም እንዳልተላከ ታውቃለህ፡፡ በሽማግሌዎች አማካይነት ከመንግስት ጋር በተደረገ ድርድር በስማችን ለሽማግሌዎች የተፃፈ ደብዳቤ ግን አለ፤ የሚል መልስ ነበር የሰጣቸው፡፡ ይህን ጊዜ አሰፋ ካሲቶ አይ ፎርሙንማ እንዳልሞላህ አውቃለሁ፤ ይኸው ፎርሙን ይዘን መጥተናል እንድትሞላው ሲለው፡ በምንም አይነት የይቅርታውን ፎርም እንደማይሞላ ነግሮት ከቢሮው ተነስቶ ሲወጣ ፕሮፌሰር መስፍን የተባለው፤ ‹ይቅርታ ዶ/ር ብርሃኑ አንድ ጥያቄ ብቻ ልጠይቅህ ለመሆኑ ይህ ፊርማ ያንተ ነው?› ብሎ ለሽማግሌዎቹ የተፃፈውን ደብዳቤና ፊርማዎች አውጥቶ ያሳየዋል፡፡ ዶ/ር ብርሃኑም አዎን ይህ ፊርማ ለሽማግሌዎች የተጻፈውን ደብዳቤ የፈረምኩበት ነው ይለዋል፡፡ በቃ ይህ ይበቃናል ብሎ ዶ/ር ብርሃኑን ያሰናብቱታል፡፡ ከዚያ በሁዋላ እያንዳንዱ እስረኛ እየተጠራ ይህ ፊርማ ያንተ ነው ወይ እየተባለ እየተጠየቀ፤ አዎን እያለ ነገሩ በዚሁ ያልቃል፡፡ በነጋታው ለሽማግሌዎች የተጻፈውን የፈረሙት እስረኞች በሙሉ ይፈታሉ፡፡

- የሆነው ይህ ነው፡፡ አስፈላጊ ያልሆኑ አንዳንድ ዝርዝሮች ተረስተው ካልሆነ በቀር፡ የቅንጅት መሪዎች የተፈቱበት ሂደት ይህን ይመስላል፡፡ ይህን እውነት እነመለስ ሰማይ ቢዘሉ፤ እስረኞቹን በሙሉ መልሰው እስር ቤት ቢያስገቡ፤ ሽማግሌ ተብየዎቹ በፍርሀት ተመልሰው እናታቸው ሆድ ውስጥ ቢገቡ የሚቀይሩት አይሆንም፡፡

***መደምደሚያ፡***

የቅንጅት መሪዎች በመጀመሪያ ከእስር ከወጡ በሁዋላ ባወጡት የመጀመሪያ መግለጫ ላይ የአፈታታቸውን ሂደት በተመለከተ በስምምነቱ መሰረት፤ ሽማግሌዎቹ መግለጫ እስከሚሰጡበት ድረስ ምንም እንደማይልና ይልቁንም ይህን መግለጫ መስጠት የሽማግሌዎቹ የሞራል ሀላፊነት እንደሆነ ገልፆ ነበር፡፡ በተለይም በስተመጨረሻው በነመለስ በኩል የተደረገው ተራ የማጭበርበር ስራ የሽማግሌዎቹን የሞራል ስብእና ነክቶት እውነቱን ለህዝብ ይነግራሉ ተብሎ ተጠብቆ ነበር፡፡ ይልቁንም በዚያን ጊዜ ስራችን ብለው የያዙት የአፈታቱን ሂደት ለዘመዶቻችን በግልፅ የነገርነውን፤ ከዚያ ጋር ተያይዞ የእነመለስን ፍፁም የወራዳነት ባህርይ የገለፅነውን ሰዎች በየቤታችን እየመጡ፤ ‹የመንግስት ሰዎች የምትሉትን እየሰሙ ተቆጥተዋል፤ ምህረቱን አንስተን መልሰን እንከታቸዋለን ብለዋል፤ ተጠንቀቁ…ወዘተ) የሚሉ ማስፈራሪያዎችን ሲነግሩን ሰነበቱ፡፡

ያኔስ ነገሩም ትንሽ ትኩስ ስለነበር፤ ውሸቱም በቶሎ እንዳይታወቅ፤ በሱ አስታኮ በቅንጅት ውስጥ ክፍፍል ለመፍጠር ፈልገው ከነበር እሱ እንዳይከሽፍባቸው ፈልገው…ወዘተ የሚሉ ምክንያቶች ልንፈጥርላቸው እንችላለን፡፡ ከአንድ አመት በሁዋላ፤ ብርቱካን የተናገረችውን፤ እኛም ከላይ ያቀረብነውን ሀቅ መናገር ለምን እንደዚህ ደማቸውን አስቆጣው? የሚለው ጥያቄ ነበር ምናልባት የጤና መታወክ ችግር ይሆን እንዴ ብለን ከላይ የውሸት በሽታን በሚመለከት አዋቂዎች የሚሉትን

በግርጌ ማስታወሻ ለአንባቢያን ለማካፈል የወደድነው፡፡ በኛ በኩል ሕመምተኞች መሆናቸው ላይ ብዙ ጥርጥር የለንም፡፡ ግን እሱ ብቻ ነው አንልም፡፡

እንደነመለስ ያሉ በሽተኛ አምባገነኖች ከእውነት ጋር ያላቸው ፀብ ከአጠቃላይ የአገዛዝ ፍልስፍናቸው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በምንም አይነት ሕዝቡ በፈቃዱ እንደማይገዛላቸው አውቀውታል፡፡ ያላቸው አማራጭ በጉልበት መግዛት ነው፡፡ ግን ጉልበት ብቻውን፣ ላለመገዛት ከቆረጠ፣ ክብር አለኝ ብሎ የሚያምን ሕዝብ ባለበትና ለዚህም ለክብራቸው ለመሞት የቆረጡ ጥቂት ጎበዞች ባሉበት፣ የማህበረሰቡ ድጋፍ ተጨምሮበት እንኳዋን የትንሽ ድሀ አገር ጥቂት ትእቢተኞችን ከዚያም በላይ ሀይል ያላቸውን ሐያላን መንግስታትን ለረጅም ጊዜ አያቆያቸውም፡፡ ይህን ፅጉፍ ስንፅፍ ወያኔ/ኢሕአዴግ በሁለት አመት ተዋርዶ ከሶማሊያ የሚወጣው ለዚህ ነው፡፡ ሶቭየቶች ከአፍጋኒስታን የወጡት ለዚህ ነው፡፡

ጉልበት በስልጣን ለማቆየት ሌላ መሳሪያ ያስፈልገዋል፡፡ የሕዝቡ ቅስም መሰበር አለበት፡፡ ለውጥ አይቻልም ብሎ ማመን አለበት፡፡ ፍፁም ተስፋ መቁረጥ አለበት፡፡ በዳዩቹን ትቶ እርስ በርሱ መናቆር አለበት፡፡ ሰውነቱን ትቶ በእንሰሳዊ ባህሪው ላይ ማተኮር አለበት፣ ለሚጠጣውና ለሚበላው ብቻ ማሰብ አለበት፡፡ እውነት የሚባል ነገር፣ ፍትህ የሚባል ነገር የለም ብቻ ሳይሆን መቼውንም አይኖርም ብሎ ማመን አለበት፡፡ ያን ጊዜ የሚፈለግበት የማጎብደድ ደረጃ ላይ ደርሶአል ማለት ነው፣ ያን ጊዜ ምንም ቢደረግ አሜን ብሎ ይቀበላል፣ ያን ጊዜ ለመገዛት ብዙ ሀይል አያስፈልገውም፡ ‹ቢጭኑት አህያ፣ ቢጋልቡት ፈረስ› የሚባለው ደረጃ ላይ ደርሶአል ማለት ነው፡፡

ሕብረተሰብን እዚያ ደረጃ ላይ ማድረስ ነው የነመለስ የረጅም ጊዜ የአገዛዝ እስትራቴጂ፡፡ የነብርቱካን አይነት፣ የነቴዲ አይነት፣ ‹የለም እያወቅኩትማ ሀሰት አልናገርም› የሚል ሰው የነመለስን አውሬነት የሚቀሰቅሰው አንድም በበሽተኛነታቸው የተቀበሉት እውነት ውሸት ነው ስለተባለባቸው በመናደድ፣ ይበልጡንም ደግሞ ይህንን ለአገዛዛቸው የሚያስፈልጋቸውን የህዝብ ቅስም መሰበር በቶሎ ተግባራዊ ለማድረግ ባለመቻላቸው የሚገጥማቸውን አበሳ በመረዳት ነው፡፡ በሁለቱም ምክንያት ግን በነሱ ላይ ልንፈርድ አንችልም፡፡ የማንነታቸው መግለጫ ነው፡፡ ለእውነት የቆሙ ኢትዮጵያውያን በበቂ ቁጥር እስካሉ ድረስ፣ ቄሶቹም ቢዋሹ፣ ሀጂዎቹም ቢቀጥፉ፣ ሽማግሌዎቹም ለእውነት መቆም ቢፈሩና የሽምግልናን ተቁዋም ቢያዋርዱ፣ የተማሩትም እውነትን የማያውቁዋት ቢመስሉ፣ እነኝህ ለእውነት የቆሙ ኢትዮጵያውያን አገራችንን መልሰው የእውነትና የህቅ መሬት እንደሚያደርጉዋት፣ የውሸት አገዛዙም እንደ እንቡዋይ ካብ እንደሚፈርስ እነሱም እኛም እናውቀዋለን፡፡

---

- [i i] የእነ መለስ ውሸት በጣም ፈጣጣ ከመሆኑ የተነሳ ልክ እንደኛው የሰዎቹን ጤንነት የምትጠራጠሩ ሳትኖሩ አትቀሩም በሚል ተራ ውሸታምና በሽተኛ ውሸታም የሚለዩበትን ነገር ሀኪሞች እንዴት ይመለከቱታል? እነኝህ ሰዎች ዝም ብለው የሚዋሹ ውሸታሞች ናቸው ወይንስ ትንሽ ጤናቸውም የተናጋ ነው? የሚለውን ነገር ለመመልከት ኢንሳይክሎፒዲያ አገላብጠን ነበር፡፡ አንባቢው የሰዎቹን ሁኔታ በራሱ አይቶ እንዲፈርድ የኢንተርኔት ኢንሳይክሎፒዲያ በጉዳዩ ላይ የሚለውን በጥሬው በእንግሊዘኛ ለማቅረብ መረጥን፡፡ እንደሚከተለው ይነበባል፡
- **Identifying a Pathological Liar**

- Pathological liars, or "mythomaniacs," may be suffering from histrionic personality disorder or narcissistic personality disorder. The following comments basically reflect a pathological liar who has the characteristics of histrionic personality disorder.

- It is very hard to tell when one is a pathological liar. Some people just are liars and lie to lie because they can and they don't care about getting caught and aware that you know they have lied. These people care not about lying, it's no big deal. It's like "ok, so what? I lied". The pathological liar on the other hand, IS aware that they are lying BUT will go to extremes to make you believe that they are truthful. They appear to believe their own lies BUT in truth, they know their lies are just that, lies. But because their efforts are constantly backing up their lies, it appears to us that they actually believe their lies, when we eventually do find out about them and then we tend to feel sorry for these people. Then they have an excuse, "I am sick, I don't know why I lie, I believed what I was saying etc." The only truth was the fact that they don't know why they lie. Other than that it's crap. It is true that most of them have an extremely low sense of self worth and are continuously trying to make themselves feel better about THEMSELVES and this is one reason they lie. It is about them but the lies are not always set up with the purpose to hurt some one else; it's that these people feel so low about themselves they need to create ANYTHING different from the ugly reality they feel about themselves so they lie about even the most tiniest little thing. The people closest to them get sucked into these lies which sometimes start as something very trivial and then turn into something that can turn everyone involved worlds upside down and inside out.

- Other indicators: 1) Rage attacks after they realize you're questioning their lies. 2) Distraction techniques, e.g. hanging up the phone when you catch them in lie, playing word games, or even just running out of the room. After using the distraction technique, or rage attack, or sometimes both, they will pretend that nothing ever happened. They re-write history, so it never did happen in their minds. Normal people do it too, but these people take it to the extreme.